**የመልካም ምኞት መግለጫ፤**

መስከረም 1 2003 ዓ.ም

**ከግንቦት 7 የፍትህ፣ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ**

እንኳን ለ2003 አዲስ ዓመት አደረሳችሁ!

አዲሱ ዓመት ለእርስዎ፣ ለቤተሰብዎና ለወዳጆችዎ የሰላም የጤና የብልፅግና እንዲሆን፣የግንቦት 7 የፍትሕ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ይመኝልዎታል፡፡

የግንቦት 7 ንቅናቄ ይህንን የአዲስ ዘመን መለወጫ በዓል ምክንያት በማድርግ ለኢትዮጵያውያን በሙሉ ወገናዊ ጥሪ ያቀርባል፡፡

ይህንን ከአለም ህዝብ ልዩ የሚያደርገንን የመስከረም 1 ቀን የዘመን መለወጫ በዓል ስናከብር ሃገራችንንም እናስባት!

ይህንን ልዩ ባህል ለእኛ ለማስተላለፍ የሃገራችንን ነጻነት ተከላክለው ለእዚህ ያበቁንን ቀደምቶቻችንን እናስብ!

ዛሬ የእዚህ ባህል ተሸካሚ የሆነው የሃገራችን ህዝብ የሚገኝበትን የመከራና የስቃይ ህይወት እናስብ!

ዛሬ የእዚህ ልዩ ባህል ማህፀን የሆነችው ሐገራችን፣ ብሄራዊ ክብሯን ባዋረዱ፣ ደህንነቷንና ህልውናዋን አደጋ ላይ በጣሉ ዓይን ያወጡ ዘረኞችና ዘራፊዎች እጅ መውደቋን እናስብ!

ለመጪው ዓመት ስለምንሰራቸው ስራዎች ቃል ስንገባ የኢትዮጵያና የሕዝቧም ጉዳይ በእዚሁ ቃል ኪዳናችን ውስጥ ቦታ እንስጠው!

አዲሱ ዓመት ሐገራችንና ሁሉንም ኢትዮጵያዊ አዋርደው ለመግዛት ቆርጠው የተነሱትን ጥቂት ዘረኞች በቃችሁ የምንለብት ይሁን!

አዲሱ ዓመት መብቱ ተገፎ በጋዛ ሐገሩ ከጎዳና ተዳዳሪ ውሻ ልዩነት የሌለውን በድህነት ሲኦል ውስጥ የሚኖረውን መብት አልባ ወገናችንን የምንታደግበት ይሁን!

አዲሱ ዓመት ኢትዮጵያን ለሁላችንም የምትስማማ ለሁላችንም የምትበጅ የሰላም፣ የብልጽግና፣ የእኩልነትና የአንድነት ረድኤት የወረደባት ሃገር ለማድረግ ሁላችንም የየራሳችንን ጥረት ለማድረግ ቆርጠን የምንነሳበት ይሁን!

የግንቦት 7 ንቅናቄ የ2003 ዓ.ም ቃል ኪዳን ይህ ነው፡፡ በእዚህ ቃል ኪዳን ሁላችንም እንተሳሰር!

የግንቦት 7 ንቅናቄን ይደግፉ፣ ግንቦት 7ን ይቀላቀሉ፡፡